# ቤቴል ቲቺንግ ጠቅላላ ሆስፒታል አመሰራረት

የዛሬው ቤቴል ቲቺንግ ጠቅላላ ሆስፒታል በዶ/ር ይገረሙ አሰፋው ፊለቀ ባለቤትነት በ1988ዓ.ም ከሜክሲኮ አደባባይ ወረድ ብሎ በኪራይ በተያዘ አንድ አነስተኛ ቪላ ቤት ውስጥ በ110,000 (አንድ መቶ አሥር ሺ ብር) ካፒታል ቤቴል የሴቴች ልዩ ክሊኒክ በሚል ስያሜ በአብዛኛው እናቶችና የሕፃናት እንክብካቤ (MCH) ዘርፍ ልዩ ትኩረት በማድረግ ሥራውን ጀመረ:: ክሊኒኩ ሥራ በጀመረበት ወቅት በተለይ የግል የጤና ተቋማት ብዙም ያልነበሩበት ጊዜ ስለነበር ከመንግሥት የጤና ተቋማት ጎን ለጎን ለኅብረተሰቡ በተለይ ለእናቶችና ለሕፃናት ሕክምና ጥራት ያለው አማራጭ አገልግሎት በመስጠት የፈር ቀዳጅነት ሚናውን ተጫውቷል::

በመቀጠልም ኅብረተሰቡ በጤና ተቋሙ ለመገልገል ያለውን ከፍተኛ ፍላጎት በመገንዘብ ከክሊኒክነት ወደ ከፍተኛ ክሊኒክነት እንዲያድግና ሁለገብ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል::

ይህ በእንዲህ እያለ የኅብረተሰቡን ከፍተኛ የጤና ችግር ዕለት በዕለት በመመልከት ሕዝቡ የተሻለ የጤና አገልግሎት ሊያገኝ የሚችልበትን ከፍተኛ የግል የጤና ተቋም ለመገንባት ማሰላሰል ተጀመረ:: ይህንኑ ራዕይ ተግባራዊ ለማድረግ በ1989 ዓ.ም በወርሃ ግንቦት ሊገነባ የታሰበውን ሆስፒታል ፕላንና የፕሮጀክት ጥናት በመያዝ ኢትዮ ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት እንዲቀርብ ተደረገ::

ለሃገር እድገትና ብልጽግና ከፍተኛ ራዕይ ያለው ይህ መሥሪያ ቤት የቀረበለትን የኢንቨስትመንት ፈቃድ ጥያቄ ወዲያውኑ ተቀብሎ ፈጸመ::

የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከተገኘ በኋላ ሆስፒታሉ የሚሰራበትን ቦታ ለመጠየቅ አስፈላጊውን ዲዛይንና የፕሮጀክት ጥናት በማዘጋጀት በወቅት የክልል 14 ሊዝ ቦርድ ለሚባለው ጥያቄው የቀረበ ሲሆን ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ በ1990 ዓ.ም መጀመሪያ

በተሰጠው በጣም አነስተኛ ቦታ ላይ የሆስፒታሉ ግንባታ ተጀመረ፡፡ ከሦስት ዓመት ግንባታ በኋላ በየካቲት ወር 1993 ዓ.ም ሆስፒታሉ ሥራውን ጀመረ፡፡

ሆስፒታሉ ግንባታ በነበረበት ወቅትና የግንባታ የግንባታ ሥራው ከተጠናቀቀም በኋላ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን የሥራ ኃላፊዎች የሆስፒታሉ ፕሮጀክት በየጊዜው የሚያቀርበው ጥያቄ ሁሉ ወቅታዊ ምላሽ በመስጠት በየጊዜው በሆስፒታሉ ግንባታ ቦታ በመገኘትና ጉብኝት በማድረግ ከፍተኛ ምክርና እገዛ አድርገውልናል፡፡ የሆስፒታሉ ግንባታ ከተጠናቀቀ በኋላም ለሆስፒታሉ የሚያስፈልግ የሕክምና መሣሪያዎች፣ አምቡላንስናና የሠራተኛ መጓጓዣ አውቶብሶች ከቀረጥ ነፃ ወደ ሃገር ውስጥ እንዲገቡ በመፍቀድ ከፍተኛ ድጋፍና እገዛ አድርጎልናል፡፡

በተጨማሪም ሆስፒታሉን ከጠቅላላ ሆስፒታልነት ወደ ከፍተኛ ቲቺንግ ጠቅላላ ሆስፒታልነት ለማሳደግ ያዘጋጀነውን የፕሮጀክት ጥናት በመመርመርና በመቀበል የጠ የቅነውን የማስፋፊያ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወዲያውኑ በመስጠት ለሥራችን ከፍተኛ የአጋርነት ሚና ተጫውቷል፡፡

ሆስፒታሉ በአሁኑ ጊዜ የውስጥ አደረጃጀቱን ለማጠናከር በሚያደርገው ከፍተኛ ጥረት የአዲስ ቴክኖሎጂ ውጤት የሆኑትን ዘመናዊ የሕክምና መሣሪያዎችን ወደ አገር ውስጥ በማስገባት አዳዲስና የተራቀቁ የሕክምና ዘዴዎችን በመጠቀም በአሁኑ ጊዜ በሌሎች በመንግሥታትም ሆነ በግል የጤና ተቋማት የሚሰጡ ከፍተኛ የሕክምና ሥራዎችን በማካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህ የአዳዲስ ሕክምና ማስፋፊያ ሥራ ሂደት ላይ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ሥራ ሂደት ላይ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ትብብርና እገዛ እጅግ የላቀ ነበር፡፡

ሆስፒታሉ ከሕክምና ሥራው በተጨማሪ የጤና ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ኮሌጅ በማቋቋሙ በጤናው ዘርፍ የሚታየውን የባለሙያዎች ዕጥረት ለማቃለል ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ኢንቨስተሩ በግል የሕክምና ሥራቸውን ሲጀምር በአነስተኛ ካፒታልና ምናልባት ከሁለትና ከሦስት ያልበለጠ የሰው ኃይል በመያዝ ሥራውን የጀመሩ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ

በክሊኒኩ፣ በሆስፒታሉና በኮሌጅ ውስጥ በባለሙያነትና በድጋፍ ሰጪነት ተቀጥረው የሚሰሩት ሠራተኞች ብዛት ከ--------------በላይ የደረሰ ሲሆን የድርጅቱ ካፒታልም ከ--------------- በላይ ሆኗል፡፡

ሆስፒታሉ ግንባታ እንዲጀምር መንግሥት የመደበለት ቦታ በወቅቱ ምን ዓይነት መሠረተ ልማት ያልተዘረጋበትና ነዋሪ ያልሰፈረበት አካባቢ ስለነበር የግንባታ ቁሳቁስ ወደ ግንባታ ቦታ ለማጓጓዝ እኳ ከፍተኛ ችግርና ፈተና ያጋጠመበት ጊዜ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ያጋጠሙን ችግሮች እጅግ በርካታ ቢሆኑም በአላማ ጽናትና ሁሉንም ችግር በመቋቋም ሥራው እንዲቀጥል በመደረጉ ዛሬ ከሆስፒታሉ ግንባትና አካባቢው ከፍተኛ ልማትና እድገት የሚታይበት ሲሆን በርካታ የንግድና የመኖሪያ ቤቶች ግንባታዎች እየተካሄደበት ይገኛል፡፡

ለዚህ አካባቢ ከፍተኛ ዕድገት የሆስፒታላችን አስተዋጽኦ ከፍተኛና ፈር ቀዳጅ መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ አካባቢው የሆስፒታላችን ስያሜ በመያዝ ቤቴል እየተባለ በመጠራት ላይ ነው፡፡

## ለወደፊቱ የሆስፒታላችን ራዕይ

♦የበለጠ የጤና አገልግሎቱን በሕክምና መሣሪያና በባለሙያ ማጠናከር

♦የጤና ኮሌጁን ለማጠናከር አሁን ከሚሰጠው የዲፕሎማ ፕሮግራም ወደ 1 ደረጃ ዲግሪ የMD እና የስፔሻሊስት ፕሮግራም አቅዷል፡፡